በአላህ ስም እጅግ አዛኝና ርህሩህ በሆነው

የኢህአዴግ መንግስት በሙስሊም ዜጎቹ ላይ እያደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ የኢትዮጵያዊያን-አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሜቴ በጽኑ አወገዘው

ዋሽንግተን ዲሲ - ጥር 04፣ 2004

በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የኢትዮጵያዊያን-አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሚቴ ኢህአዴግ በሙስሊም ዜጎቹ ላይ እያደረገ የለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ በጣሙን አሳዝኖታል። የኢትዮጵያ መንግስት መጤ የአምልኮ አስተሳሰብን በሙስሊሞች ላይ ለመጫን በሚያደርገው ሙከራን ላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃውንና ውግዘት እየገለጸ ቢሆንም መንግስት ግን በማን አለብኝነት የአገሪቱን ሀብት በመጠቀም በዚህ አፍራሽ ተግባሩ በሐይል እየገፋበት ይገኛል። ይህንኑ አስከፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ለአለም ህዝብ ለማሳዎቅና ለማውገዝ የኢትዮጵያዊያን-አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሚቴ ባለፈው ህዳር 11፣ 2004 ከአሜሪካው ቤተ መንግስት በስተጀርባና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ፊት ለፊት የተዋጣለት ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጉ ይታወሳል። በተጨማሪም ኮሚቴው በተለያዩ የአለምችን ክፍሎች ለሚገኙ በርካታ ተቋማት ዲፕሎማሲያዊ ደብዳቤዎችን ልኳል።

በአሜሪካው ድምጽ ዘገባ መሰረት የሙስሊሞች ብቸኛ የትምህርት ተቋም በሆነው አወሊያ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመማር ሁለንተናዊ መብታቸው ተገፏል። በዚህ እውቅ ተቋም ውስጥ የመማርና ማስተማር ሂደት ላይ መጤ የአምልኮ ዘይቤን በመቀየጥ ስርዓተ-ትምህርቱን ለመቀየር የሚያደርገውን ሴራ በመቃዎምና በተቋሙ ዉስጥ ያለውን አፈና ለማስቀረት የአወሊያ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው በቅጥር ግቢ ውስጥ ከሳምንት በላይ የተቃውሞ ድምጻቸውን እያሰሙ ይገኛሉ። መንግስት በቅርቡ በዘረፋ የወሰደው አወሊያ የትምህርት ተቋም ለሀምሳ አመታት ለሚጠጋ ረጂም ጊዜ ግልጋሎት የሰጠ የህዝብ ተቋም ነው። የአወሊያ የአመራር አካላትና ስራተኞች የኮሌጅ ዲኑን ጨምሮ ያለምንም ማስጠቀቂያና የስራ ፍለጋና የአገልግሎት ክፍያ ሳይሰጣቸው ከስራ ተባረዋል።

በበዲር ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (ቢ.ቢ.ኤን) እና ሰለፊያ ጋዜጣ ዘገባ መሰረት ሙስሊም ወጣቶችና የሀይማኖት አስተማሪዎች በአይነ ቁራኛ ክትትል ይደረግባቸዋል። ከየቤቶቻቸው በአፈና ይወሰዳሉ፣ በስራና በእምነት ማዕከሎቻቸው ከፍተኛ የማሸማቀቅና የማዋረድ አስከፊ ተግባራት ይፈፀምባቸዋል፤ ለአሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ሰለባ እየሆኑ ነው። ብዙ ሰዎች የደረሱበት እንደማይታወቅ ይነገራል፤ ሌሎች ደግሞ ለበርካታ ቀናት ለምን እንደተያዙ እንኳን ሳይነገራቸው ይታሰራሉ፣ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለብቻቸው ተነጥለዉ የሚታሰሩት እንየተበራከቱ ነው። ይህ ገደብ የለሽ በደልና ጭቆና በሙስሊሙ ላይ ብቻ ሳይሆን በሰፋት በኢትዮጵያዊያን ላይ ኢህአዴግ የሚፈፅመው ተግባር ነው ብሎ ኮሚቴው ያምናል።

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን በአጠቃላይ በመጤ የአምልኮ ዘይቤ አስገድዶ የማጥመቁ ዘመቻ ይህ ነው በማይባል የአስከፊና የአንገብጋቢነት ደረጃ ላይ ደርሷል። ለምሳሌ የመንግስት ሰላዮችና ካድሬዎች ስብስብ ነው ተብሎ የሚታመነው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ - መጅሊስ - በቅርቡ ወደ ደቡብ ወሎ - አማራ ክልል - ይዞት የተጓዘው ጥምር የልዑካን ቡድን እውቅ የሆኑ እስላማዊ ምሁራንን (ዑለማዎች) እና የሙስሊም ማህበረሰብ መሪዎች ከፊር (እምነት የለሽ) ናቸው ሲል አዉጇል። ይህ ደግሞ ሰላማዊ በሆነው ህዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ግራ መጋባትን፣ ድንጋጤን፣ ብጥብጥንና አለመረጋጋትን በአጭሩ ሽብርን ፈጥሯል።

የኢትዮጵያዊያን - አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሜቴ ብሩህ ተስፋ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለፍትህ፣ ለእኩልነት እና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ በሚያደርጉት የትግል ሂደት ዉስጥ በጽናት ከጎናቸው እንደሚቆም ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያዊያን - አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሚቴ ኢትዮጵያዉያን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በአንድነታቸው እንዲጸኑና፣ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለከት ያጣውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ እንዲቃወሙ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያዊያን - አሜሪካዊያን ሙስሊም አስተባባሪ ኮሚቴ የኢህአዴግን ሀላፊነት የጎደለው፣ ቅጥ ያጣ ጭካኔና ግፍ በጽኑ ያወግዛል። የአወሊያ ተማሪዎች በሰላማዊ መንገድ ለፍትህ የሚያደርጉትን ትግል በአገር ዉስጥም ይሁን ባህር ማዶ የሚገኘው የሙስሊም ማህበረሰብና መላው ኢትዮጵያዊ በጥምረት ከጎናቸው እንዲቆሙና እንዲደግፏቸው ኮሚቴው ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያዊያን - አሜሪካዊያን ሙስሊሞች አስተባባሪ ኮሜቴ